የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No.22
ADDIS ABABA 8[th] March, 2011

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፯፻፭/፪ሺ፫ ዓ.ም

ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ሲስተም ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፯፻፵፱

Proclamation No. 705/2011

African Development Fund Loan Agreement for the Electricity Transmission System Improvement Project Ratification Proclamation.... Page 5749

አዋጅ ቁጥር ፯፻፭/፪ሺ፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ሲስተም ማሻሻያ ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፺፫ሚሊዮን፯፻፶ሺ ዩኒት አፍ አካውንት /ዘጠና ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ሲስተም ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፭/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION No. 705/2011.

A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding 93,750,000 U.A (Ninety Three Million Seven Hundred Fifty Thousand Units of Account) for financing the Electricity Transmission System Improvement Project was signed in Addis Ababa on the 20[th] day of December 2010;

WHEREAS the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7[th] day of February, 2011;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for the Electricity Transmission System Improvement Project Ratification Proclamation No. 705/2011"

፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 2100150023451 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፺፫ሚሊዮን፯፻፶ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /ዘጠና ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No.2100150023451 signed on the 20th day of December 2010, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 93,750,000 U.A (Ninety Three Million Seven Hundred Fifty Thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. Effective Date.

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 8th day of March, 2011

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA